# <u>ክህደት ውሸት--ግንቦት 7 አበቃለት!</u>

## <u>አደመ በላቸው</u>

ነጋ ጠባ የሚገርመኝ ጉዳይ--ብዙ ዓመት አለፈ--ሰው እንዴት ደግሞ ደጋግሞ እንደሚታለል ነው ። የግንቦት 7 ቡድን ደጋፊዎችና አባላት በዚህ በኩል ሊጠየቁም ይገባቸዋል ። ወያኔን አጥብቀው የሚጠሉ ወጣቶች የግንቦት 7ን ምላጭ ምላሶች ሊቋቋሙ ስላልቻሉ የብርሃኑ ነጋና የጡት አባቶቹ ተደናጋሪ ሆነዋል ። ይህ ግን አሁን ማብቃት ያለበት ነው።

ጋሼ ጌታቸው ረዳን ዕድሜውን ያርዝመውና ገና ከጠዋቱ ብርሃኑ ነጋ ብሎ ቆራጥ መሪ በሚል ሲያስጠነቅቀን ነበር ። ግንቦት 7 በሰዎቹ የተቋቀመው ትግል ለማካሄድ አይሆን ትግልን ለመፈና ለማደናቀፍ ሲባል ማን ያዳገታቸው በአሁኑ ጊዜ ግልጽ ሊሆንላቸው ችሏል ። የሰምኑ ኢሳያስ ቤዛችን ጩኸት ደግሞ ይንን ይበልጥ እንድናውቅ አድርጓል ።የብርሃኑ ነጋና አንዳርጋቸው አሰግድ ሰልፋቸው ከማን ጋር እንደነበረ ሁሉም ያውቃል ። ለረጅም አንዳርጋቸው ሲሻለው አሁን ደግሞ ዓመታት ወያኔን ሲደግፉና ወያኔም ለስልጣን ሲደርስ ከመለስ ዜናዊ ጋር በሰማዕታትና ፕሮፌሰር አሥራት መሳይ ታጋዮች ላይ ሲሳለቁ የነበሩ ናቸው ። የአንዳርጋቸውን አማራው ሕዝብ ከየት ወደየትና ቆይቶ የብርሃኑ ጓደኛ የሆነው የሻዕቢያው ሰላይ ተስፋዬ ገብረአብን ዘረኛ ጽሁፎች ማስታወስ ይበቃል ። የብርሃኑ ከወያኔ ጎራ ለየት ያለ ስምሪት የተባለውም  ህብረትን ለማፍረስና ቀጥሎም ቅንጅትን መበታተን መሆኑ ማንም የሚረሳው አይደለም ። ግንቦት 7 ሲያሰኘው ሲከድ ሲያምረው ደግሞ ኢሳት የድርጅቴ ነው ብሎ ብርሃኑ ሲለፍፍ ቆይቶ ዛሬ በማያውላዳ መንገድ ኢሳት የተባለው ተቋም የግንቦት 7ና የሻዕቢያ መሳሪያ መሆኑ ተጋለጠ ። ለመሆኑ ጋዜጠኞቹ የሚባሉት ለዚህ ሙያ ብቃት ያላቸው ናቸው ? አቶ መሳይ የተባለው ቦርጩን ዘርግቶና ዝናር ጥይት ተሸክሞ የወታደር ተቋም ጋዜጠኛ ሊመስል ያደረገው ጥረት አስቂኝ ከመሆን አልፎ ያሳዝናል፤ያስገምታል ። ቀደም ሲል አንዳርጋቸው አሰግድ እንደ ኢሳያስ የመሰለ ዴሞክራት የለም ሲል ብዙ ሕዝብን ያሳዘነ ከንቱ ሙገሳ አሰምቶ ነበር ። ይህ ኤርትራን ገደለ የተባለለት አረመኔ እየከሰረ ሲመጣ የስድስት ሰዓት ቃል መጠይቅ መስጠቱና ኢትዮጵያውያንን ለማደናገር መሞከሩ የተለመደ ነው ።እነ ኤልያስ ክፍሌም አሰምተውን ነበር--ጀሌዎቹ ሳሉ ። የኢሳቶቹ ደግሞ በዛና ያንኑ እጅ እጅ ያለ ልፈፋውንና ኢትዮጵያ ድሮ አልነበረችም ጫጫታውን ቀድተውለት እነሆ ኢትዮጵያውያንን ያሳሳቱ መስሏቸው ራሳቸውን እያዋረዱ ናቸው ፡፤ አያ ጮሌው ብርሃኑ ለሻዕቢያ ቢያድርም፤ የነግብጽን ገንዘብ ቢልፍም የፈሪ ፈሪ መሆኑ በአሜሪካ ክኒን አልተቀየረምና እንኳን ኤርትራ አፍሪካም ብቅ ብሎ አያውቅም ። በዚህ አንዳርጋቸው የሚሻለው ይሆናል። በአሁኑ ዙር ደግሞ ንዓምን የተባለው ይህን ሚና ይጫወት ዘንድ ተመድቧል ተብሏል። ከንቱ ልፋት !

ግንቦት 7 ለሕዝብ ስንቴ ቃል ገብቶ ስንቴስ አፍርሷል ብንል መልሱ አያሌ ጊዜ የሚል ነው ። አሁን ደግሞ ጦር አለኝ፤ ከአርበኞች ግንባር ጋር ተዋሃድኩ ይላል ። ከአፋር ሕዝባዊ ፓርቲና ሊሎች ጋር ተደረገ የተባለው ጥምረት የት ደረሰ? ስንት የተጮኸለት ከነከማል ገልቹ ጋርስ የተደረገው ግንባር ? ሁሉም በየጊዜው የሚፈለፈል ማደናገሪያ። ግንቦት 7 ጦር መሰረትኩ ካለን ስንት አመት አለፈ? ዴምህት እንደሚባለው የምትሃት የስንት ሺ "ጦር" --አንዲት መንደርም በትግራይ ሳያጠቃ ዓመታት ያለፉት--ዓይነት ሌላ ውሸት ። ሻዕቢያ እሳት ይዟል ለወዳጁ ሆኖ የአርበኞችን ግንባር አማራ ብሎ አኮስምኖ የያዘ፤ አመራሩን የገደለና ደብዛውን ያጠፋ አሁንም የነቃ የበቃ ጸረ ኢትዮጵያ ሀይል ነው ። ሻእቢያ አነግንም ከፍፍሎ አክስሟል። ታዲያ ኮሌኔል ታደሰ ተይዞ ደብዛው ሲጠፋ መፈንቅለ

መንግስት (በኢሳያስ ላይ!) ሊያደርግ ሞክሮ ነው የተያዘው ብሎ አስተባባዩ ማን ነበር?የግንቦት 7ኡ አንዳርጋቸው ጽጌ!ሲዝረከረክ የተያዘ ወይም ያዙኝ ብሎ የገባ ቦቅባቃ! ጀሌዎቹም (ስሙ ደግሞ እንግሊያዊ ተብሎ አንዲ ሆኗል!!) በጉጠት ቢቦጭቁት ሆነ ሌላ ምስጢር የማያወጣ ብረት ነው ብለው በለፈፉ ማዕግስት ሲለፍፍ ተደብድቦ ነው አሉና ይህም የማያሳምን ሲሆንና ወያኔ እንደፎከረው ምንም ሳይገረፍ የተጠየቀውን ብቻ ሳይሆን ያልተጠየቀውን ሲለፍፍ አንዲ ጀግናውን ልደት አክብሩለት ወደሚለው ቀልድ እመር ብለው ተሸጋገሩ ። አንዳርጋቸው ጽጌ ወኔ ቢኖረው ኖሮ ከዚህ ሁሉ ቅሌት በፊት ራሱን ያጠፋና ምስጢር ከነበረም ባላጋለጠ ነበር ። በጣም የሚደንቀው የግንቦቴዎች ክርክር ደግሞ ታዲያ ምን ያድርግ?ራሱን ሊገል ነበር? የሚለው ነው ። ራሱን መግደልማ ሲያንሰው ነው ። ስንቱን ከሚያስጠቃ ወይም ከሚያስጠፋ! ግንቦት 7 ግን ምስጢር ክሌለው ፤ የሚጋለጥ የህቡዕ አባል ከሊለው--ወሬ ብቻ ነው እንደሚባለው ከሆነ--አንዳርጋቸው እስር ለጤናም ጥሩ ነው ፤ ጥሩ ይዘውኛል እያለ ደበበ እሸቱ በተጓዘበት የቆሻሻ ቱቦ መዳሁ ይሻለዋል ማለት ነው ። እያደረገ ያለውም ይህንኑ ነው ።

የግንቦት 7 የሕዝብ ንቀት ዋጋ መክፈያው ጊዜ በቡድኑ መጥቶበታል ። ኢትዮጵያን ለኢሳያስ አሳልፎ መስጠቱ ግልጽ ሆኗል ። ኢሳት የግንቦት 7ና አልፎም የኢሳያስ መሳሪያና ራዲዮ መሆኑም ማረጋገጫ አግኝቷል ። ለትግል ይበጃል ብለው ግንቦት 7ን የደገፉ ዜጎች የብርሃኑን ከንቱነትና ከሃዲነት አውቀው ራሳቸውን ከዚህ ግለሰብና ከሻዕቢያ ማራቅ ፤ ማግለል ይጠበቅባቸዋል ፡፡ኢሳያስ ኢትዮጵያን የጎዳና ያደማ፤የኤርትራን ሕዝብም ያሰቃየ፤ ስንቱን ጋዜጠኛና ጓዶቹን ሳይቀር በኮንቴነር ከቶ ያሰቃየና የገደለ፤ አሁንም ጸረ አማራ ጸረ ኢትዮጵያ አምባገነን ነው ። ባንዳ እኮ የተባለው ለሙሶሊኒ ግራዚያኒ እጁን ሰጥቶ ያደረው ዜጋ ነው ። ሻእቢያ በማያከራክር ደረጃ የኢትዮጵያ ጠላት ሆኖ እያለ፤ ኢትዮጵያ ድሮም አለነበረችም ብሎ አሁንም የሚያቅራራው ሻዕቢያ የኢትዮጵያ ህዝብ አጋር ሊሆን መቼም ሆነ ከቶም አይችልም ። ወያኒና ሻዕቢያ ከመጣላታቸው (?) በፊት ሻዕቢያ ኢትዮጵያን ሊበዘብዝና የመቶ ዓመት የቤት ሰራ ሊሰጥ ያደረገውን ሁሉ አንረሳውም ። በኢትዮጵያ መሬት ስንቱን ተቃዋሚ አፍኖ ገድሏል። የኢትዮጵያን ዛፍና ወርቅም ዘርፏል። የጥይት ክምችታችንንም አጋይቷል ። የሀሰት ብርም አምጥቶ ኤኮኖሚያችንን ጎድቷል ። ከዚያም ባድሜን ወሮ ለመቶ ሺ ሰው በላይ ሞት ተጥያቂ ሆኖ ቆይቷል ። ከዚህ ሌአስ በየመን ና ላማፓዱሳ፤በሳይናይና ሊቢያ የሚያልቁት ስደተኞችስ የማን ሰለባ ናቸው ? ሻዕቢያ አጋር ሳይሆን መወገድ ያለበት መጥፎ ጠላት ነው ።

የሕዝብ ደርጅቶች የሕዝቡ አገልጋይ ናቸው እስከተባለ ድረስ ትሁትነትም ይጠበቅባቸዋል ። ዋሾው ብርሃኑ ነጋ ጠባ አዳዲስ ውሸት እየፈበረከ ሳያፍር ህዝብን ማደናገር ይጥራል ። ህዝብ ሁሉ የጠላውን የአፍቅሮ ሻዕቢያ ፖለቲካውን አሳምሮ ለማቅረብ ሲጥር ለከት የለውም ። አምባገነን  መቅረብ ብርቅ የሆነባቸው አሳፋሪ ጋዜጠኞች ተብየው ለኢሳያስ ሲስግዱና ሲልፈሰፈሱ ማየቱ ውርደት ሆኖ ሳለ ትልቅ ጋዜጠኝነት ነው ብለው ውዳሴ ከንቷቸውን ለቀውብናል ። መሳይና ፋሲል እንዲሁም መቶ አለቃ ሲሳይ አጌና ከሚዲያው መራቅ አለባቸው--ከስረዋል፤ከሽፈዋል፤ ክብር የላቸውም፤ራሳቸውን በሕዝብ ፊት ደግመው ደጋግመው አዋርደዋል ፡፡ በስድስት ወር አዲስ አበባ እንገባለን ተባለ? ባዶ ቀረ። በ 500 ዶላር ክፍያ አርበኛ መባልም የሚል ማሾፈአይ መጥቶ ተዋሆች ገዘባቸውን ተበልተው ቀሩ። የግንቦት 7 ህዝባዊ ጦር ተባለ--ያውም በአምስት ዙር የሰለጠነ--ደብዛው እስካዝሬ ጠፍቶ ጥቂት የሆኑትን የአርበኞ ግንባር ምልምሎች ላይ መጣበቁ የግድ ሆነው ። እንኳን የወያኔን መደበኛ ጦር ቀርቶ ሁልት ሶስት ክብሪቶችና ጋንታዎቹን የሚገጥም ሀይል ግንቦት 7ም ሆነ የተዋሃዱት የላቸውም ፡፤ቪዲዮ

ሲሆን የሚሰታቸው ከባድ መሳሪያም ቪድዮው ሲጠፋ መሳሪውም ወደ ሻእቢያ የሚመለስ ነው ። ወደ ኢሳት ስንመለስም ዛሬ የኢትዮጵያ ጠላቶች የሚባሉትን ሁሉ መደረክ ሰጪ ይህ ተቋም ነው ። በተለይ ገንጣይና ተገንጣዮችን። ያን መርዘና የሻዕቢያ ሰላይ ተስፋዬ ገብረ "ሰይጣንን"፤ ያን አሁን የገንዘብ ሌባ የተባለውን የጥላቻ ረጪ ጃዋርን፤ ስንቱን የደርግ ነፍሰ ገዳይና ከመንግስቱ ጭምር...የሰለቸንን የሀሰት ቋት ራሱን ብርሃኑን .መድረክ ሰጪ ኢሳት ነው ።

እስከዛሬ ግንቦት 7 ሲያታልለን ቆየ ። በቃ! እንበለው አሁን ምክንያቱም ከፖለቲካ ንግድና ጨዋታ የሀገርን ህልውና በተመለከተ ለሻዕቢያ አድሮ ሀገራችንን ሊያስጠፉ ስለተነሳ፤የሻዕቢያ መሳሪያ ሆኖ ብቅ ስላለ በዝምታና በቸልታ ልናልፈው አንችልም ። የሀገር ማዳን ግዳጅ ነው፤ኢትዮጵያን ከጥፋት ለማዳን ። ውስጥ ለውስጥ የትግራይ ትግሪኚ ግብ ለመድረስ ወያኔና ሻዕቢያ መተባበራቸውን ከእኔ በላይ ጉድዩ የሚያውቁ የተናገሩት ነው ። በእኔ ብጤ ደረጃ ግን ሳየው--ስናየው--ግን 24 ዓመት ሙሉ ወያኔም እረዳልሁ ያለእ የሻዕቢያ ተቃዋሚ ወይም ሻዕቢያ እደግፈዋለሁ ያለው የወያኔ ተቃዋሚ--ማንም--የረባ ትግል ለማካሄድ አለመቻሉና በሁቱም ሀይሎች ይልቁንም መሻጠሩ የታየ ነው ። ግንቦት 7 የሻዕቢያ መሳሪያ ሆኖ ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን ለማዳከምና ለማፍረስ ቢሰራ እንጂ ወያኔንማ አያሳስበውም። ይህ ያየነው ሀቅ ነው ። በነብርሃኑ መሪነት ብቅ የሚል ጦር ካለ ቅቅቅቅቅ በሚልነው ወያኔ የሚቀበለው። ከግንቦት 7 ለኢትዮጵያ የሚበጅ ነገር ይመነጫል ብለው አሁንም የሚሞኙ ካሉ በቃችሁ እንበላቸው ።ለመሆኑ ግንቦት 7 ከዚህ ከዚያ የሚቃርመውን ገንዘብ የሚመረምር ኦዲት አለ? የብርሃኑን ውሸት--ወደ ወንጀል ቢፈረጅ የሚገባው የሆነውን--በቃህ አንተ ዋሾ ብሎ የሚያጋልጥ ይጥፋ? ሲዋሽ መቀበል፤ መነዳትና አሁን ደግሞ ሻዕቢያን የኢትዮጵያ ወዳጅ ብሎ ሲያቀርብ እሺ ብሎ መቀበል ኢትዮጵያን መካድና መጉዳት ነው ። መጫወቻ አንሁን ለሻዕቢያ ካልን ራሳችንን ከነብርሃኑና ቡድኑ እናርቃለን ።

በቃን ውሸት!

ሻዕቢያ የኢትዮጵያ ጠላት ነው !!!